# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

## የ6ኛ ክፍል ከተማ አቀፍ አንደኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና

## ሂሳብ, ሰኔ 2017ዓ.ም/ JUNE 2025 G.C

**የጥያቄ ብዛት: 30** **የተፈቀደው ሰዓት: - 1 ሰዓት**

**አጠቃላይ ትዕዛዝ**

ይህ የሂሳብ ፈተና ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ 30 ጥያቄዎች ተካተዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል። የፈተና ትእዛዞችን በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል።

መልስ የሚሰጠው በተናጥል በተዘጋጀው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው ። በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛው መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው። ትክክለኛውን መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት። የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት።ለምሳሌ የጥያቄው መልስ “መ” ቢሆን በዚህ መልኩ አራተኛው ክብ መጥቆር አለበት።

| ሀ | ለ | ሐ | መ |
|---|---|---|---|
| ○ | ○ | ○ | ● |

ፈተናውን ሰርቶ ለመጨርስ የተፈቀደው 1 ሰዓት ነው። ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የተጠቀማችሁበትን እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናው መስራት ማቆም አለባችሁ ። ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችሁ ተቀምጣችሁ መጠበቅ አለባችሁ ።

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰአት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል።

ፈተናውን መስራት ከመጀመራቹሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሙላት አለባችሁ ።

**ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !**

LIVEWORKSHEETS

**ትዕዛዝ፡** ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡ አራት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ብቻ በመምረጥ የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ አጥቁር/ሪ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ የፈሳሽ ቁሶች መለኪያ ምድብ አሃድ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ሳንቲ ሜትር    ሐ. ግራም

ለ. ሜትር ካሬ    መ. ሚሊ ሊትር

2. አንድ ዝርግ ወለል ርዝመቱ 5ሜ እና ወርዱ 3ሜ ነው። የዚህ ወለል ስፋት ስንት ነው?

ሀ. 2ሜ$^2$.    ሐ. 8ሜ$^2$

ለ. 15ሜ$^2$    መ. 20ሜ$^2$.

3. የስሌት $\frac{3}{4} - \frac{2}{5}$ ውጤት ስንት ነው?

ሀ. $\frac{7}{20}$    ሐ. $\frac{17}{20}$

ለ. $\frac{7}{10}$    መ. $\frac{23}{20}$

4. የሁለት ዛፎች ርዝመት 23.38ሜ እና 12.62ሜ ከሆነ፤ የዛፎቹ ጠቅላላ ርዝመት ስንት ሜትር ይሆናል?

ሀ. 10.51    ሐ. 35.75

ለ. 10.76    መ. 36.00

5. ከድር 3.75 እና 0.08 አባዛ። ከድር ያገኘውን ውጤት በክፍልፋይ ሲገልጽ ስንት ይሆናል?

ሀ. $\frac{3}{10}$    ሐ. $\frac{9}{4}$

ለ. $\frac{19}{5}$.    መ. $\frac{3}{1}$



LIVEWORKSHEETS

6. ከሚከተሉት አገላለጾች ውስጥ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. $\frac{1}{4} = 2.5\%$      ሐ. $\frac{1}{2} = 5\%$

ለ. $\frac{1}{8} = 1.25\%$      መ. $\frac{3}{4} = 75\%$

7. የአልጀብራዊ መግለጫ ሸ+5ቀ+ሸ−2ቀ−2ሸ ሲቃለል ውጤቱ የቱ ነው?

ሀ. 3ቀ      ሐ. 2ሸ+3ቀ


ለ. 2ሸ−3ቀ      መ. 2ሸ

8. አንድ ያልታወቀ ቁጥር በሦስት ተባዝቶ ሰባት ሲደመርበት ሃያ ሁለት ቢሆን፤ ያልታወቀው ቁጥር ስንት ይሆናል?

ሀ. 2      ሐ. 4

ለ. 3      መ. 5

9. በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ዕድሜ ቀጥሎ በቀረበው ባር ግራፍ ተገልጿል።




በጠቅላላ የክፍሉ ተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

ሀ. 20      ሐ. 28

ለ. 24      መ. 30



LIVEWORKSHEETS

10. ሁለት ባለ ነጠብጣብ ኪዩቦች ወደ ላይ ቢፈነጠሩ፣ ተደምረው 7 የሚሰጡ ቁጥሮችን የማግኘት ዕድላችን ስንት ስንተኛ ነው?


ሀ. $\frac{5}{36}$

ሐ. $\frac{1}{6}$

ለ. $\frac{5}{6}$

መ. $\frac{1}{9}$

11. ቀጥሎ የቀረበው ጠጣር ምስል ምን ተብሎ ይጠራል?



ሀ. ፒራሚድ

ሐ. ኮን

ለ. ፕሪዝም

መ. ሲሊንደር

12. ዝርግ አንግል ሲገመስ፤ ልኬቱ ምን ያህል ይሆናል?

ሀ. $360^0$

ሐ. $90^0$

ለ. $180^0$

መ. $45^0$

13. የአንድ ካሬ ስፋት 100 ካሬ ሜትር ቢሆን፤ የካሬው የአንዱ ጎን ርዝመት ስንት ሜትር ነው?

ሀ. 5

ሐ. 25

ለ. 10

መ. 40



LIVEWORKSHEETS

14. ርዝመቱ 5 ኪ.ሜ እና ወርዱ 15ሜ የሆነን መንገድ አስፓልት ለማልበስ በቀን 500ሜ ርዝመት ያለው አስፓልት ይሠራል። መንገዱን ሙሉ በሙሉ አስፓልት ለማልበስ ስንት ቀን ይፈጃል?

ሀ. 20

ለ. 15

ሐ. 10

መ. 5

15. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ውስጥ ለ6 ተካፋይ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. 248

ለ. 348

ሐ. 448

መ. 548

16. የ 720 ብቸኛ ትንትን የሆነው የቱ ነው?

ሀ. $2^3 \times 3^2 \times 5^2$

ለ. $2^4 \times 3^2 \times 5^2$

ሐ. $2^4 \times 3^2 \times 5$

መ. $2^4 \times 3 \times 5$

17. የ 45 እና ሌላ ሙሉ ቁጥር ትልቁ የጋራ አካፋይ (ት.ጋ.አ) 9 ነው። የሁለቱ ቁጥሮች ትንሹ የጋራ ብዜት (ት.ጋ.ብ) 90 ቢሆን፣ ሁለተኛው ሙሉ ቁጥር ስንት ይሆናል?

ሀ. 9

ለ. 18

ሐ. 36

መ. 54

18. የክፍልፋይ $\frac{32}{176}$ ዝቅተኛ ሒሳባዊ ቃል የቱ ነው?

ሀ. $\frac{4}{22}$

ለ. $\frac{4}{11}$

ሐ. $\frac{2}{11}$

መ. $\frac{1}{11}$



LIVEWORKSHEETS

19. ከአከታሚ አስርዮሽ 0.125 ጋር እኩል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. $\frac{1}{40}$

ለ. 1.25%

ሐ. 125%

መ. $\frac{1}{8}$

20. አንድ ነጋዴ ቴሌቭዥን በ12000 ብር ገዝቶ በብር 15000 ቢሸጥ፤ የነጋዴው ትርፍ በፐርሰንት ምን ያህል ነው?

ሀ. 25%

ለ. 20%

ሐ. 75%

መ. 11%

21. የስሌት $3.25 \div \frac{25}{8}$ ውጤት የቱ ነው?

ሀ. 1.00

ለ. 1.04

ሐ. 1.40

መ. 10.40

22. የመቁጠርያ ቁጥር 2010000 በአስር ርቢ ብዜት ሲገለጽ ምን ይሆናል?

ሀ. $201 \times 10^4$

ለ. $20.1 \times 10^5$

ሐ. $0.201 \times 10^7$

መ. $2.01 \times 10^6$

23. ከስብስብ {0፣1፣3፣4፣5፣6} ውስጥ የያለእኩልነት ዓረፍተ ነገር 2ሽ+6<12 መፍትሄ የትኞቹ ናቸው?

ሀ. 0 እና 1

ለ. 0፣1 እና 3

ሐ. 3 እና 4

መ. 4፣5 እና 6



LIVEWORKSHEETS

24. በሙሉ ቁጥሮች ስብስብ ውስጥ የያለእኩልነት ዓረፍተ ነገር $ሽ-3 \leq 1$ መፍትሄ ስብስብ የቱ ነው?

ሀ. {0፣1፣2፣3}

ሐ. {0፣1፣2፣3፣4}

ለ. {1፣2፣3፣4፣5}

መ. {4፣5፣6፣7፣...}

25. በ37.5 ግራም የቀይ ጤፍ እንጀራ ውስጥ 4.2 ግራም ፕሮቲን 0.6 ግራም ቅባት፣ እና 32.7 ግራም ካርቦሃይድሬት ቢኖረው፤ 250 ግራም የቀይ ጤፍ እንጀራ ውስጥ በአጠቃላይ ምን ያህል ፕሮቲን እና ቅባት ይኖራል?


ሀ. 28 ግራም

ሐ. 218 ግራም

ለ 32 ግራም

መ. 222 ግራም

26. ቀጥሎ በተሰጠው ምስል ውስጥ ለ እና መ ትይዩ ቀጥታ መስመሮች ናቸው፡፡ ረ ደግሞ ቆራጭ ቀጥታ መስመር ነው፡፡




ከሚከተሉት ጥንድ አንግሎች ውስጥ ፍርቅ ውጫዊ የሆኑት የትኞቹ ናቸው?

ሀ $<2$ እና $<7$

ሐ. $<4$ እና $<6$

ለ. $<1$ እና $<6$

መ. $<1$ እና $<4$



LIVEWORKSHEETS

27. ከሚከተሉት ሶስት የልኬቶች ዝርዝር ጎነ-ሶስት ሀለመ የሚመሰርተው የቱ ነው?

ሀ. ሀለ=2ሳ.ሜ፣ ለመ=9ሳሜ፣ ሀመ=6ሳ.ሜ

ለ. ል(<ሀ)= $80^0$፣ ል(<ለ)= $108^0$፣ ለመ=6ሳ.ሜ

ሐ. ሀለ= 3ሳ.ሜ፣ ለመ= 4ሳ.ሜ፣ ሀመ= 5ሳ.ሜ

መ. ል(<ሀ)= $40^0$፣ ል(<ለ)= $108^0$፣ ል(<መ)= $22^0$

28. የሬክታንግላዊ ፒራሚድ እና የጎነ-ሶስታዊ ፒራሚድ የሚመሳሰሉበት ባሕርይ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የመሰረት ቅርጽ

ለ. የጎን ጠርዞች ብዛት

ሐ. የገጾች ብዛት

መ. የጎን ገጾች ቅርጽ

29. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ <u>ያልሆነው</u> የቱ ነው?

ሀ. ምልከታ ማድረግ

ለ. ከተመዘገበ ማጣቀስ

ሐ. አሻሚ ጥያቄ መጠየቅ

መ. ሙከራ ሰርቶ መጻፍ

30. በአንድ ክፍል ውስጥ ያሉ 20 ተማሪዎች ዕድሜ 8፣ 12፣ 14 እና 16 ሲሆን፤ የእነዚህ ተማሪዎች ብዛት በቅደም ተከተል 8፣ 3፣ 5 እና 4 ነው፡፡ ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ሐሰት የሆነው የቱ ነው?

ሀ. አማካይ 11

ለ. ሚዲያን 8

ሐ. ሞድ 8

መ. ሬንጅ 8



LIVEWORKSHEETS